**Ethiopian Journal of Business and Social Science**
**Available online at:** https://survey.amu.edu.et/ojs/index.php/EJBSS/issue/archive
**Volume: 3 Number: 2 , 2020 , Pages: 67~81**
**ISSN:2707-2770**

# አዕምሯዊ የመማር ብልሐቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት የማሻሻል ሚና፤ በሰባተኛ ክፍል ተተኳሪነት

***ፀጋነሽ ዮሴፍ[1] እና ኃይላይ ተስፋይ ገብረማርያም[2]***

***Article Info***

*Accepted on January, 2020*
*Received in revised form: May,2020*
*Published on: December, 2020*

***©Arba Minch University, all rights reserved***

## አህጽሮተ ጥናት

የጥናቱ ዓላማ አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት የማሳደግ ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ዓላማውን ለማሳካት በ*2011* ዓ.ም በወላይታ ሶዶ ከተማ በጊዮርጊስ ትምህርት ቤት በመማር ላይ የሚገኙ የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ኢአፍፈት ተማሪዎች ሦስት መማሪያ ክፍሎች በአመቺ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ ተሳታፊዎቹ በብልሃት *42*፣ በብልሃትአልባ *38* እና በቁጥጥር *38* በድምሩ *118* ሲሆኑ፣ በአንብቦ መረዳት ፈተናና በማንበብ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቆች አማካይነት መረጃ ሰጥተዋል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ *(*በባለሁለት ተላውጦ ልይይትና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ*)* ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ውጤቶችም በብልሃትና በብልሃትአልባ አቀራረቦች የተማሩት በተለመደው የማንበብ ትምህርት ከተማሩት ይልቅ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ጉልህ መሻሻል አሳይተዋል፡፡ ነገርግን በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ጉልህ ሚና አላሳዩም፡፡ በብልሃትና በብልሃት አልባው ቡድን መካከልም የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ጉልህ ልዩነት እንደሌለ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ከሁለቱ የብልሃት አቀራረቦች አዕምሯዊ ብልሃትን በይዘትነትና በትግበራ መማርና በትግበራ ብቻ መማር ልዩነት እንደሌለው ያሳያል፡፡ ስለዚህ ትግበራው በሁለቱም ቡድኖች ስለሚገኝ በይዘትነት ከመማር ይልቅ በትግበራ መማር አስተዋፅኦ እንዳለው ያመለክታል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡**- አዕምሯዊ የመማር ብልሐቶች፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ የማንበብ ተነሳሽት፣ የአማርኛ ኢአፍፈት፣ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች

---

[1]በደቡብ ክልል፣ ወላይታ ዞን፣ ሶዶ ከተማ አስተዳደር፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህርት ናት፤ tsegetch2009@gmail.com

[2]በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ የማኅበራዊ ሳይንስና ስነሰብዕ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽfhፍ-ዐማርኛ ትምህርት ክፍል፣ ረዳት ፕሮፌሰር ነው፤ *hailay.tesfay@amu.edu.et*

## 1. መግቢያ

ማንበብ ከፅሁፍ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ መቻል ነው፡፡ Harmer (1991) እንደሚገልፁት፣ ማንበብ በዐይንና በአዕምሮ የሚከናወን ተግባር ነው፤ ዐይን ከተፃፈው ፅሁፍ መልዕክትን ማየት ሲያስችል፣ አዕምሮ ደግሞ ዐይን ያየውን መልዕክት በመገንዘብ ትርጉም ይሰጣል፤ ምላሽም ያዘጋጃል፡፡ በዚህም ማንበብ የተፃፈን ፅሁፍ መልዕክት ማየት ብቻ ሳይሆን፣ በጽfhፍ ውስጥ የሰፈረውን መልዕክት መረዳት ዋና የማንበብ ተግባር ነው፡፡ Khezrlou (2012) እንደሚገልፁትም፣ ማንበብ የተፃፈን ነገር ከዳር እስከዳር ማዳረስ ሳይሆን፣ ማጤንን፣ ማስተዋልንና መመርመርን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ስነልሳናዊና አዕምሯዊ የሆኑ ውስብስብ ነገሮችን አዋህዶ የያዘ ነው፡፡ በተጨማሪም ማንበብ በፀሀፊውና በአንባቢው መካከል የሚደረግ ተግባቦት ነው፡፡ ይህም ፀሀፊው ሀሳቡንና መረጃውን በፅሁፍ ያሰፍራል፤ አንባቢው ደግሞ በፅሁፍ ውስጥ የሰፈሩትን መረጃዎች ይቀበላል (Yaman & Cakici, 2013)፡፡ ይህን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ Yussof, et al (2012) ንባብ ፀሀፊውንና አንባቢውን የሚያገናኝ የተግባቦት መንገድ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይም ማንበብ አዕምሯዊና ማህበራዊ ተግባራት አቀናጅቶ የያዘ በመሆኑ ማገናዘብን፣ ማስታወስን፣ ማመሳሰልን፣ ማጠቃለልን፣ ትኩረት መስጠትንና መገምገምን ስለሚያጠቃልል በትምህርት ሊዳብር ይገባል፡፡

የማንበብ ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ቁልፍ ጉዳይ ነው (Duke & Pearson, 2009)፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን መጋቢው (2009) ሲገልፁት፣ በፅሁፍ ውስጥ የቀረቡ አዳዲስ መረጃዎችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ሀሳቦቸውን መገንዘብ መቻል ነው፡፡ እንዲሁም አንብቦ መረዳት አእምሯዊ ሂደቶችን በማለፍ የሚዳብር ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ አንብቦ መረዳት በፅሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መገንዘብ ወይም መረዳት ሲሆን የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባል (Griffiths & Cansiz, 2015; Ur, 1996; Yaman & Cakici, 2013)፡፡ ሙሉገበያ (2009) አንብቦ መረዳት የአንድን ፅሁፍ ሀሳብ አዕምሯዊ ዕውቀትና ስነልሳናዊ ችሎታ በማጣመር ለፅሁፉ ትርጉም መስጠት፣ ዐውዳዊና ከዐውድ ውጭ የሆኑ ፍችዎችን መገንዘብን ያጠቃልላል፡፡ አንብቦ መረዳት አዕምሯዊ ክዋኔ ብቻ ሳይሆን ስሜታዊ ተግባር ጭምር ነው፡፡ ተማሪዎች ለሚያነቡት ነገር ስሜት የሚሰጡት በማንበብ ክዋኔያቸው የሚከሰቱ አዕምሯዊና ስሜታዊ ተግባር ጥምረት በመሆኑ የማንበብ ተነሳሽነት ማጣት ለአንብቦ መረዳት መሰናክል ነው፡፡ ስለዚህ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በአግባቡ እንዲዳብር በብልሃት የታገዘ የትምህርት አቀራረብ እንደሚያስፈልግ የአፍልቆታውያን ሆነ የግንባታውያን የመማርና የማስተማር ሞዴል ያመላክታሉ፡፡

ቋንቋን የመማር ብልሃት ለቋንቋ መማር ማስተማር ዋነኛና ጠቃሚ መሳሪያ ነው፡፡ Griffiths (2004) ቋንቋን የመማር ብልሃት ተማሪዎች አንድን ዕውቀት ለማግኘት ሊጠቀሙ የሚችሏቸው የመማሪያ ዘዴ ወይም መሳሪያ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ እንደ Oxford (1990) አገላለፅ ደግሞ፣ ቋንቋን የመማር ብልሃት ተማሪዎች አዲስ ነገር እንዲያገኙ፣ እንዲያደራጁ፣ ችግር እንዲያቀሉና መረጃ እንዲያገኙ የሚረዳና የሚያለግል አሰራር ነው፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎች የተወሰነ ድርጊት የያዘ፣ መማርን ቀላል፣ ፈጣን፣ አስደሳች፣ በራስ የሚመራ፣ ውጤታማና አዲስ መረጃ እንዲተላለፍ ያደርጋል (Anne, 2014; Griffiths, 2015) ፡፡

በዚህም የተለያዩ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች እንዳሉ የቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች (ለምሳሌ፣ Cohen, 1999; Oxford, 1990; 2003) ይገልጻሉ። ከብልሃቶቹ አንዱ አዕምሯዊ ቋንቋን የመማር ብልሃት ነው። Oxford (1990) በሚገልጹት መሠረት፣ አዕምሯዊ ቋንቋን የመማር ብልሃት ተማሪዎች የሚማሩትን ነገር ለመረዳትና ለመጠቀም የሚያግዝ ነው። እንዲሁም ተማሪዎች እንዲማሩት የታለመውን ቋንቋ በመደጋገም፣ በመተንተን ወይም በማጠቃለል የሚከውኑበት ነው። እንደ O'malley & Chamot (1990) ገለፃ፣ አዕምሯዊ ብልሃቶች አንድ ዘዴ ለአንድ ተግባር የሚከናወንበት ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች መረጃን ለማግኘት፣ ለመጠቀም፣ ለማዳበርና ችግርን ለማቃለል የሚጠቅምና የሚቀሰቅስ ነው (Oxford, 1990; 2003) ።

ዘውዱ (2008) እንደሚገልጹት፣ የማንበብን አዕምሯዊ ብልሃቶች ማስተማር ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ አንብበው በመረዳት ሂደት ውጤታማና ብልህ አንባቢዎች እንዲሆኑ ይረዳሉ። Griffiths (2004), O'malley & Chamot (1990) እና Shew (2017) በበኩላቸውም፣ አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ወቅት አዕምሯቸውን በመጠቀም አንድን ተግባር ለማከናወን፣ ለመጨረስ፣ የሚገጥማቸውን ችግር ለመፍታት የሚያግዙ አጠቃላይ ሁኔታዎችን ነባራዊና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለመገልገል ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ለማብላላት፣ ለመረዳት፣ ለመተንተን በቀጥታ ሆን ተብሎ የሚተገበር ነው። እንዲሁም አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች አዕምሯዊ ድርጊትን የሚያመለክት ነው።

በሌላ አገላለጽ አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች የተማሪዎችን ትግበራ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የመማር አቅም ያሳድጋል። Cohen (1999) አዕምሯዊ ብልሃት በሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን፣ ሀረጋትን በአዕምሮ በመያዝ፣ በማከማቸት፣ በመደጋገም ይከናወናል በማለት ይገልፃሉ። እንደ Omalley & Chamot (1990), Oxford (1990) እና Richards & Lockhart (1994) አገላለፅ፣ አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪው አንድን ነገር እንዴት እንደሚረዳ፣ እንደሚያስታውስ፣ እንዲያውቅና አዕምሯዊ ምስል እንደሚከስት፣ አዕምሯዊ የሆነ ግብን ለማሳካት የሚደረግና የትምህርት ተግባራትን በራስ ለመስራት የሚያስችል ብልሃት ነው። እንዲሁም ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ በቀጥታ በመገልገል ተረድቶና አፍልቆ ለመጠቀም ያስችላሉ።

በመሆኑም፣ ይህ ጥናት አዕምሯዊ ብልሃቶችን መማርና የማንበብ ትምህርትን በአዕምሯዊ ብልሐቶች ታግዞ እንዲቀርብ ማድረግ በዐማርኛ ቋንቋ ኢአፍፈት ተማሪዎች አንብቦ በመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነትን በማሳደግ ያለውን ሚና ውጤታማ መሆን አለመሆኑን መርምሯል።

## 2. የጥናቱ መነሻ ምክንያት

የማንበብ ክሂል ትምህርት የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ያዳብራል። መጋቢው (2009) እንደሚገልፁት፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲዳብር ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር፣ ስለሌሎች ለማወቅ፣ የረቀቀ አስተሳሰብን ለማጎልበትና ከዓለም ህዝብ መረጃ ለማግኘት ትልቁን ድርሻ ይይዛል። በመሆኑም ይህን ጉልህ ፋይዳ ለማረጋገጥም ሆነ አዳዲስ ገጽታዎች ለመመርመር በዓለማችንም ሆነ በሀገራችን በአንብቦ መረዳትና በአዕምሯዊ ብልሃቶች ላይ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች (ለምሳሌ፣ በጎሰው፣ 2003፤ Anne, 2014; Chanyalew & Abiy, 2015; ዘውዱ፣ 2008) አሉ።

የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ለማሳደግ ከመዳዳት በመነጨ ብዙ ተመራማሪዎች (Chanyalew & Abiy, 2015; እንድሪስ፣ 2009፤ ሙሉገበያ፣ 2009፤ Teshale & Yemanebrhan, 2015; ዘውዱ፣ 2008፤) የተለያዩ የመማርና የማስተማር ብልሐቶችን በመጠቀም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት መርምረዋል። ዘውዱ (2008) በኢትዮጵያ የሚሰጠው የማንበብ ትምህርት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና ተነሳሽነት የማያሳድግና የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ሂደትን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ይገልፃሉ። በጎሰው (2003) በአዲስ አበባ ከተማ የነባርና የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ላይ ባደረጉት ጥናት የነባርም ሆነ የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል ትምህርት አሰጣጥ ደካማና መሻሻል የሚገባው እንደሆነ አመላክተዋል። Teshale & yemanebrhan (2015) በቦንጋ መምህራን የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች የንባብ ልምምድ ፍተሻ አድርገው አብዛኞቹ ተማሪዎች ከቃል ትርጉም ደረጃ ንባብ ውጭ ብልሃትን ዘዴን መሰረት ያደረገ የንባብ ሂደት በመተግበር እንዳልተጠቀሙ ያሳያሉ። Chanyalew & Abiy (2015) የመምህሩ ድጋፍ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና ፈትሸው ድጋፍ የተሰጠው የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ተማሪዎችን አንብቦ ለመረዳት ውጤታማ በመሆኑ፣ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ስለድጋፍ ሰጪ የማስተማሪያና የመማሪያ ስልጠና በስፋት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል። የሙሉገበያ (2009) ጥናት የፅሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ፈትሿል። ውጤቱም የፅሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ያሳያል። እንድሪስ (2005) በደቡብ ወሎ ዞን በሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የንባብ ፍላጎት፣ የንባብ ልምድ፣ የጥናት ክሂሎችና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ መርምረው የማንበብ ብልሃቶችን በአግባቡ ተገንዝበው በተለያዩ መንገዶች ማንበብን መከወን አለመቻላቸው የማንበብ ልምድ እንቅፋት መሆኑን አሳይተዋል።

በLau & Chan (2003) ጥናት የማንበብ ብልሃት ዕውቀትና የመጠቀም ችሎታ ከአንብቦ መረዳትና ከተነሳሽነት ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸውና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ እንደሆኑም ተገልጹዋል። የYussof, et al (2012) ጥናት ደግሞ አዕምሯዊና ንድፋዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሳደግ ከግንባታውያን አተያየት አንጻር የተሰራው ፍትነት መሰል ጥናት አዕምሯዊና ንድፋዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን እንደሚያሳድግ አሳይቷል። የAnne (2014) ጥናት አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃት መጠቀም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሳደግ ያለው ሚና እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች (EFL) የተሰራው ጥናት፣ ከአዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶች ውስጥ የትኛው አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃት ውጤታማ መሆኑን ለማሳየት ነበር። ጥናቱም አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶች በጥምረት ደጋግሞ መስራት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ደካማ ለሆኑ ተማሪዎች ይበልጥ ውጤታማ እንደሆነ አሳይቷል። በመሆኑም አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶችንና አገልግሎታቸውን መማር እንዳለባቸው ጠቁመዋል። የSuyitno (2017) እና Shew (2017) ጥናቶች አዕምሯዊ ብልሃቶችን መጠቀም ለአንብቦ መረዳት ችሎታና ለውጤት ያለው አስተዋፅኦ በእንዶኖዢያ ቋንቋ በተፃፉ ምንባቦች ላይ መርምሯል። ውጤቱም ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና ውጤት የብልሃቶች አመራረጥ ትኩረት

ሊሰጠው እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡ ማለትም፣ ለራሳቸው የሚሆነውን (የማንበብ ልምድ ያላቸውና የሌላቸው ተማሪዎች መርጠው መጠቀም አለባቸው)፡፡ ምክንያቱም አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡

በተለይ ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው የሀገር ውስጥ ጥናቶች (እንድሪስ፣ 2009፤ የዘውዱ፣ 2008) ማንበብን በመማር የተለያዩ ብልሐቶች በአንብቦ መረዳትና በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያላቸውን ፋይዳ በመፈተሽ ላይ አተኩረዋል፡፡ የእንድሪስ (2009) የቴክስት ውቅር ብልሃቶች ማንበብን መማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ውጤት፣ የማንበብ ተነሳሽነት፣ የማንበብ ግለ ብቃት እምነትና ትኩረት እንደሚያሻሽል በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡ የዘውዱ (2008) ጥናት፣ ተማሪዎችን የሚና ለዋጭ ዘዴ አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶችን በማስተማር፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውንና የማንበብ ተነሳሽነታቸውን ለማሳደግ አስተዋፅኦ እንዳለው በግልፅ አሳይቷል፡፡

ነገርግን ከላይ ያየናቸው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቀደምት ጥናቶች ለአንብቦ መረዳት አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ሂደትን፣ ብልሃትን መሰረት ያላደረገ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ስለዚህ ክፍተቱን ለመሙላት በብልሃት ማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል፡፡ እንዲሁም ከአዕምሯዊ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች አኳያ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ሚና ለዋጭ አዕምሯዊ ብልሃቶችን መማር ለአንብቦ መረዳት ችሎታ አስተዋፅኦ እንዳለው (ለምሳሌ፣ ዘውዱ፣ 2008) ያሳያሉ፡፡ ይሁን እንጂ አዕምሯዊ ብልሃቶች ለአንብቦ መረዳት እንጂ ለተነሳሽነት ያላቸውን ሚና አልዳሰሱም፡፡ በመሆኑም አዕምሯዊ ብልሃቶች በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ለመፈተሽ ብልሐቶቹን ማስተማርና በማንበብ ሂደት መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የእንድሪስ (2009) እና የዘውዱ (2008) ጥናቶች በዐማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ናቸው፡፡ በዚህም ቀደምት ጥናቶቹ አዕምሯዊ ብልሃቶቹን ቀድሞ ማስተማርና በማንበብ ሂደት መተግበር ለአንብቦ መረዳትና ለተነሳሽነት ያላቸውን ፋይዳ አልፈተሹም፡፡ ለዚያም አዕምሯዊ ብልሃቶችን ማስተማርና መተግበር ለአንብቦ መረዳትና ለተነሳሽነት ያላቸውን ሚና መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት የአዕምሯዊ ብልሐቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያላቸውን ሚና በመመርመር ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

1. የአዕምሯዊ ብልሃቶች ይዘትና በአዕምሯዊ ብልሐቶች የታገዘ የማንበብ ትምህርት የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ኢአፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ከተለመደው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ የተለየ ሚና አላቸውን?
2. የአዕምሯዊ ብልሃቶች ይዘትና በአዕምሯዊ ብልሐቶች የታገዘ የማንበብ ትምህርት የሰባተኛ ክፍል ኢአፍፈት ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማሳደግ ከተለመደው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ የተለየ ሚና አላውን?
3. አዕምሯዊ ብልሐቶችን በይዘትነት የተማሩና የተገበሩ (በብልሃት የተማሩ)፤ በአዕምሯዊ ብልሐቶች ትግበራ(በብልሃት አልባ) የማንበብ ትምህርት ከተማሩ የሰባተኛ ክፍል ኢአፍፈት ተማሪዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት አላቸውን?

## 3. የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ አእምሯዊ ብልሃቶች የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ሚና መመርመር ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም፣ ጥናቱ የተከተለው ንድፍ ፍትነት-መሰል (Quasi Experimental) ሲሆን፣ የትግበራው ሂደት በሦስት ተሳታፊ ቡድኖች የተመሰረተ ነው።

### 3.1. የጥናቱ ተሳታፊዎች

ጥናቱም ያተኮረው በወላይታ፣ ሶዶ ከተማ አስተዳደር በሚገኘው የጊዮርጊስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በ2011 ዓ.ም በሰባተኛ ክፍል በተማሩ 118 ተማሪዎች ላይ ነው። ትምህርት ቤቱ አመቺ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል። ምክንያቱም የትምህርትቤቱ መምህራን በጥናቱ ትግበራ ዕቅድ መሠረት ለማስተማር ፍቃደኛ ስለሆኑ ጥናቱን በአግባቡ ለመተግበር ያስችላል። በትምህርት ቤቱ በመማር ላይ የሚገኙ የሰባተኛ ክፍል ቡድኖች ስድስት (ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ እና ረ) ሲሆኑ የአፍፈትና ኢአፍፈት ተማሪዎችን ለመለየት የአጠቃላይ መረጃ መጠይቅ ቅጽ ሞልተው ከተገኘው መረጃ በብዛት ኢአፍፈት ተማሪዎች የሚገኙባቸውን ሦስት ቡድኖች (ሀ፣ ለ እና ሐ) ተመርጠው በጥናቱ ተሳትፈዋል።

### 3.2. የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቅ ነው። የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናው ሃያ ጥያቄዎችን ይዞ ሶስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል አስር የምርጫ ጥያቄዎች፣ የሁለተኛው ክፍል አምስት የእውነት/ሀሰት ጥያቄዎች፣ የሶስተኛው ክፍል አምስት ክፍት ቦታ የመሙላት ጥያቄዎች የያዘ ነው። የፈተናውን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራንና በጥናቱ አማካሪዎች ግምገማ ተደርጓል። እንዲሁም የቅድመ ትምህርቱና የድህረ ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ፈተናው ከክፍል ደረጃው ጋር አቻ በሆኑ 30 ተማሪዎች ላይ ቅድመ ሙከራ ፍተሻ (Pilot) ተደርጎ በክሮንባክ አስተማማኝነት መገመቻ .789 መሆኑ ተረጋግጧል። ከዚያም የመለካት አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ጥያቄዎች በውስጣዊ ተዛምዶ በመረጋገጣቸውና ከመምህራን ግምገማ በመነሳት በተወሰኑት ጥያቄዎችላይ ማሻሻያና እንዲወገዱ ተደርገው የጥናቱ ተሳታፊዎች ተፈትነዋል።

በዚህ ጥናት የማንበብ ተነሳሽነትን ለመለካት የፅሁፍ መጠይቅ ተግባራዊ ተደርገጓል.፤፤ የፅሁፍ መጠይቁ 30 ዝግ ጥያቄዎችን አሉት፣ የተዘጋጀው ከዘውዱ (2008) ሃምሳ ሶስት የማንበብ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑትን በመውሰድ (ተሻሽሎ) ነው። የፅሁፍ መጠይቁ ለተማሪዎች እንዲሞሉት ከመቅረቡ በፊት ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በአማካሪዎች ተገምግሟል። እንዲሁም የቅድመ ትምህርቱና የድህረ ትምህርቱ የፅሁፍ መጠይቅ ከክፍል ደረጃው ጋር አቻ በሆኑ ተማሪዎች ላይ ቅድመ ሙከራ ፍተሻ (Pilot) ተደርጎ በክሮንባክ አስተማማኝነት መገመቻ ውጤቱ .720 መሆኑ ተረጋግጦ ለተማሪዎች ተሰጥቷል።

### 3.3. የጥናቱ ሂደቶች

የዚህን ጥናት አላማ ለማሳካት በመጀመሪያ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የማረጋገጫ ደብዳቤ በመያዝ ከተመረጠው ትምህርትቤት አስተዳደር፣ የዐማርኛ መምህራን፣ በናሙናነት ከተመረጡት 118 ተማሪዎችና ከወላጆቻቸው ጋር በጥናቱ አላማ ዙሪያ ውይይት ተደርጎ ፍቃደኝነታቸውም ተረጋግጧል። በመቀጠልም በናሙናነት ከተመረጡት ሦስት ክፍሎች በዕጣ ንሞና የቁጥጥር፣ የብልሃትና ብልሃት አልባ ቡድን ተመርጧል። ለአሰልጣኝ መምህር በአቀራረቡ ዙሪያ ለሁለት ቀን ለሁለት ሰዓት በዋና አጥኚዋ መምህር ስልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም መረጃዎቹ የሚሰበሰቡበትና ተጠኚ ተማሪዎችቹ የሚማሩበትን አመቺ ቀን ተወሰኗል። መረጃዎቹ በሚሰበሰቡበት ሂደት በሚፈጠሩ ችግሮች ምክንያት የመረጃ መዛባት እንዳይከሰትና በጥናቱ ማጠቃለያዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎች እንዳይፈጠሩ፣ እንዲሁም የጥናቱ ግኝቶች ተገቢነት የሌላቸው እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ተደርጓል።

ከዚያም ተማሪዎቹም በተያዘላቸው ቀን የቅድመትምህርት የፅሁፍ መጠይቆችንና የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችን ተፈትነዋል። የፅሁፍ መጠይቆቹ በትክክል ስለመሞላታቸው፣ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች በትክክለኛው መንገድ ስለመመለሳቸው ለማረጋገጥ የማጣራት ስራ ተከናውኗል። አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶችን ለመማር ውህድ አሀዶች ከመማሪያ መፅሃፍና ከልዩ ልዩ ምንጮች በመፈለግ በአጥኚዋ ተዘጋጅተው በመምህራንና በአማካሪ መምህራን ተገምግመው ከመጋቢት ሃያ ስድስት እስከ ሚያዚያ ሃያ ስምንት ለአራት ሳምንታት ከክፍለ ጊዜ ውጪ በሳምንት አንድቀን ለሁለት ሰዓታትና በመደበኛ ሰዓት በሳምንት ለሁለት ክፍለጊዜ (80 ደቂቃ) በአጠቃላይ ለአስራ ሶስት ሰዓታት ከሃያ ደቂቃ ሲሆን በክፍለጊዜ ሲከፋፈል ለሃያ ክፍለጊዜ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ተምረዋል። በመቀጠልም በሚያዝያ ሃያ ዘጠኝ የድህረትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ተፈትነዋል። የማንበብ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቅ ሞልተዋል። መረጃዎቹ የማጣራት ስራ ተከናውነዋል።

## 4. የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት መረጃዎች በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በአንብቦ መረዳት ፈተናና በማንበብ ተነሳሽነት ጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል። በመሣሪያዎቹ የተገኙትን መረጃዎች ለመተንተን አስፈላጊ የሆኑት የመረጃ አተናተን ስልቶች ተመርጠዋል። መረጃዎቹም የጥናቱን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ተተንትነዋል። ለስታትስቲክሳዊ ስሌቶቹ ፍተሻ የጉልህነት ደረጃ $p < 0.05$ ነው። በያንዳንዱ ስታትስቲክሳዊ ስሌት ፍተሻ የተካሄደው እንደየመተንተኛ ዘዴዎቹ ባህርይ እሙኖች መሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው።

በመጀመሪያ የብልሃት፣ የብልሃት አልባና ቁጥጥሩ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት በአንብቦ መረዳት ፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነዋል። የቅድመ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳት ፈተናውና የፅሁፍ መጠይቁ ውጤት ትንተና ዓላማ ሶስቱ ቡድኖች በብልሃት፣ በብልሃት አልባና በተለመደው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ከመማራቸው በፊት ጉልህ ልዩነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የተከናወነ ሲሆን የድህረ ትምህረቱ ትንተና ዋና ዓላማ በሶስቱም ቡድኖች በብልሃት፣ በብልሃት አልባና በተለመደው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩ በኋላ ጉልህ የአማካይ ውጤት ልዩነት ማስመዝገብ አለማስመዝገባቸውን ለማረጋገጥ የተከናወነ ነው። በዚህ መሰረት የመጀመሪያው የጥናቱ ጥያቄ ለመመለስ መረጃዎቹ በሰንጠረዥ1 እና 2 ተመልክቷል።

**ሠንጠረዥ 1፡-** የብልሃት፣ የብልሃት አልባውና የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት አማካይ ውጤቶች ንፅፅር ባለሁለት ተላውጦ ትንተና ልይይት

| ቡድን | ናሙና (*n*) | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የልይይት ዋጋ (*F*) | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 9.619 | 3.478 | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 9.658 | 3.988 | .027 | 2,115 | .973 |
| ቁጥጥር | 38 | 9.474 | 3.431 | | | |

በሠንጠረዥ1. የቡድኖቹ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ድርብ ገፅታ ልይይት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ መረጃውም በባለሁለት ተላውጦ ልይይት ተሰልቶ፣ ውጤቱ ($F$ (2, 115) = .027, $p$ = .973) በሦስቱ ቡድኖች ቅድመትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል፡፡ ይህም ሶስቱም ቡድኖቹ በተለያዩ አቀራረቦች ማንበብን ከመማራቸው በፊት አንብቦ የመረዳት ችሎታ መሠረታዊ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡-** የብልሃት፣ የብልሃት አልባ ቡድን ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት አማካይ ውጤቶች ንፅፅር ባለሁለት ተላውጦ ትንተና ልይይት

| ቡድን | ናሙና (*n*) | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የልይይት ዋጋ (*F*) | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት መጠን | የጥንካሬ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 11.833 | 3.192 | | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 11.816 | 4.989 | 4.6 | 2,115 | .012 | .074 |
| ቁጥጥር | 38 | 9.500 | 3.302 | | | | |

በሠንጠረዥ 2. በድህረ ትምህርት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ የተገኙ መረጃዎች ያስገኙት ውጤት፣ በባለሁለት ተላውጦ ልይይት ተሰልቶ፣ ውጤቱ ($F$ (2, 115) = 4.6, $p$ = .012, $\eta 2$ = 0.74) ሆኗል፡፡ ይህም በቡድኖቹ ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል፡፡ የጉልህ ልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም በከፊል ኤታ ስኴር ተሰልቶ መካከለኛ ($\eta 2$ = 0.74 (7.4%)) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሁለተኛው የጥናቱ ጥያቄ ጥያቄውንም ለመመለስ መረጃዎቹ በሰንጠረዥ 3 እና 4 ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 3.፦** የብልሃት፣ የብልሃት አልባውና የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶች ባለሁለት ተላውጦ ትንተና ልይይት

| **ቡድን** | **ናሙና (*n*)** | **አማካይ ውጤት** | **መደበኛ ልይይት** | **የልይይት ዋጋ (*F*)** | **የነጻነት ደረጃ** | **ጉልህነት መጠን** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 3.403 | .535 | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 3.476 | .406 | 2.045 | 2,115 | .134 |
| ቁጥጥር | 38 | 3.605 | .388 | | | |

በሠንጠረዥ 3 የተገኘው ውጤት በባለሁለት ተላውጦ ልይይት ተሰልቶ ውጤቱ ($F$ (2, 115) = 2.045, $p$ = .134) ሆኗል። ውጤቱም በሦስቱ ቡድኖች ቅድመትምህርት የማንበብ ተነሳሽነታቸው መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል። ይህም ሶስቱም ቡድኖቹ በተለያዩ አቀራረቦች ማንበብን ከመማራቸው በፊት በማንበብ ተነሳሽነታቸው ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል።

**ሠንጠረዥ 4፦** የብልሃት፣ የብልሃት አልባውና የቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶች ባለሁለት ተላውጦ ትንተና ልይይት

| **ቡድን** | **ናሙና (*n*)** | **አማካይ ውጤት** | **መደበኛ ልይይት** | **የልይይት ዋጋ (*F*)** | **የነጻነት ደረጃ** | **ጉልህነት መጠን** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 3.712 | .501 | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 3.591 | .406 | .781 | 2,115 | .460 |
| ቁጥጥር | 38 | 3.646 | .382 | | | |

በሠንጠረዥ 4. መረጃውም በባለሁለት ተላውጦ የልይይት ትንተና ተሰልቶ፣ ውጤቱ ($F$ (2, 115) = .781, $p$ = .460) ሆኗል። ይህም በሦስቱ ቡድኖች ድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነታቸው ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል። ይህም ሶስቱም ቡድኖቹ በተለያዩ አቀራረቦች ማንበብን ከተማሩ በኋላ በማንበብ ተነሳሽነታቸው ጉልህ ልዩነት እንደሌላቸው አሳይቷል። ሶስተኛው ጥያቄ የቅድመ ትምህርቱ ውጤት ሠንጠረዥ 5 የድህረ ትምህርቱ ውጤት ሠንጠረዥ 6 ተጠቃለው ቀርበዋል።

**ሠንጠረዥ** 5፡- የፍትነት (የብልሃትና የብልሃት አልባ) የቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት አማካይ ውጤቶች ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| **ቡድን** | **ናሙና (*n*)** | **አማካይ ውጤት** | **መደበኛ ልይይት** | **ቲ ዋጋ (*t*)** | **የነጻነት ደረጃ** | **ጉልህነት መጠን** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 9.619 | 3.478 | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 9.658 | 3.988 | .047 | 78 | .963 |

በሠንጠረዥ 5. የሦስተኛው ጥያቄ ለመመለስ የቅድመትምህርት ውጤት፣ መረጃውም ባለሁለት ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ፣ ውጤቱ ($t\,(78) = .047$, $p = .963$) ሆኗል። በሁለቱ ቡድኖች ቅድመትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል። ይህም ሁለቱም ቡድኖቹ በተለያዩ አቀራረቦች ማንበብን ከመማራቸው በፊት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል።

**ሠንጠረዥ 6** ፡- የፍትነት (የብልሃትና የብልሃት አልባ) ቡድኖች የድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት አማካይ ውጤቶች ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| **ቡድን** | **ናሙና (*n*)** | **አማካይ ውጤት** | **መደበኛ ልይይት** | **ቲ ዋጋ (*t*)** | **የነጻነት ደረጃ** | **ጉልህነት መጠን** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 11.833 | 3.192 | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 11.816 | 4.986 | .019 | 78 | .985 |

በሠንጠረዥ 6. ድህረትምህርት የአንብቦ መረዳት መረጃውም ባለሁለት ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ፣ ውጤቱ ($t\,(78) = 0.019$, $p = 0.985$) ሁለቱም ቡድኖች ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል። ይህም ሁለቱም ቡድኖቹ በተለያዩ አቀራረቦች ማንበብን ከተማሩ በኃላ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል።

**ሠንጠረዥ** 7፡- የፍትነት (የብልሃትና የብልሃት አልባ) ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶች ንፅፅር በባዕድ ናሙና ተ-ቴስት

| **ቡድን** | **ናሙና (*n*)** | **አማካይ ውጤት** | **መደበኛ ልይይት** | **ቲ ዋጋ (*t*)** | **የነጻነት ደረጃ** | **ጉልህነት መጠን** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 3.403 | .535 | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 3.476 | .406 | - .802 | 78 | .425 |

የሠንጠረዥ 7. ውጤት፣ መረጃውም ባለሁለት ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ፣ ውጤቱ ($t$ (78) = -802, $p$ = .425) በሁለቱ ቡድኖች ቅድመትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አመኖሩን አሳይቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖቹ በተለያዩ አቀራረቦች ማንበብን ከመማራቸው በፊት በማንበብ ተነሳሽነታቸው ልዩነት እንደሌላቸው አሳይቷል፡፡ በመቀጠልም በድህረ ትምህርት የተሰበሰቡ የፍትነት (የብልሃትና የብልሃት አልባ) ቡድኖች ድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 8፡-** የፍትነት (የብልሃትና የብልሃት አልባ) ቡድኖች ድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤቶች ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| **ቡድን** | **ናሙና (*n*)** | **አማካይ ውጤት** | **መደበኛ ልይይት** | **ቲ ዋጋ (*t*)** | **የነጻነት ደረጃ** | **ጉልህነት መጠን** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ብልሃት | 42 | 3.712 | .501 | | | |
| ብልሃት አልባ | 38 | 3.591 | .404 | .436 | 78 | .664 |

የሠንጠረዥ 8 መረጃውም ባለሁለት ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ፣ ውጤቱ ($t$ (78) = .436, $p$ = .664) በሁለቱም ቡድኖች የድህረ ትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል፡፡ ይህም ሁለቱም ቡድኖቹ በተለያዩ አቀራረቦች ማንበብን ከተማሩ በኃላ በማንበብ ተነሳሽነታቸው ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡ በዚህም አዕምሯዊ ብልሐቶች በይዘትነት ተምሮ በመተግበርና (በብልሃት የተማሩ) በአዕምሯዊ ብልሐቶች ትግበራ ብቻ (በብልሃት አልባ) የማንበብ ትምህርት መማር በተማሪዎች መካከል የተሻለ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት እንደሌለው አሳይቷል፡፡

## 5. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አዕምሯዊ ብልሃቶች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት የማሳደግ ሚና መመርመር ነበር፡፡ የጥናቱን ዋና ዓላማ ለመፈተሽም ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎችን በመቅረጽ የጥናቱ ሂደት በሶስት ቡድኖች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በጥናቱ ሂደትም የቅድመና የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ ከመረጃዎቹም የተገኙት ውጤቶች እንደአይነታቸው በባለሁለት ተላውጦ ትንተና ልይይት፣ ባለሁለት ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱም የመጀመሪያ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መረጃዎቹ በድርብ ገፅታ ልይይት ተተንትኗል፡፡ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም በአዕምሯዊ ብልሐቶች የታገዘ የማንበብ ትምህርት የተማሩት ሁለቱ የሙከራ (የብልሃትና የብልሃት አልባ) ቡድን ተማሪዎች ድኅረትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት በተለመደው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩት የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ውጤት በልጦ ልዩነት አሳይቷል፡፡ የጥንካሬ ደረጃውም በከፊል ኤታ ስኴር ተሰልቶ መካከለኛ ($\eta 2$ = 0.74 (7.4%)) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አእምሯዊ ብልሃቶችን መማርና መተግበር የተማሪዎችን

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል ጉልህ ሚና ያለው መሆኑን ነው። የዚህ ጥናት ውጤት ግኝትም Anne (2014); Yaman & Cakici (2013); Suyitno (2017); Khezrlou (2012); Lau & Chan (2003); Yusfarina, et al. (2012) አዕምሯዊ ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ የላቀ ድርሻ እንዳለው ካገኟቸው የጥናት ውጤቶች ጋር ተደጋጋፊነት አለው። በጥቅሉ አዕምራዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ከተለመደው የማንበብ ማስተማሪያ አቀራረብ የበለጠ ውጤታማ መሆኑን የዚህ ጥናት ግኝት አሳይቷል።

ሁለተኛው የጥናቱ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መረጃውም በባለሁለት ተላውጦ ትንተና ልይይት ተተንትኗል። ($F$ (2, 115) = .781, $p$ = .460) ሆኗል። የተገኘውም ውጤት እንዳሳየውም በአዕምሯዊ ብልሐቶች የታገዘ የማንበብ ትምህርት የተማሩት ሁለቱ የሙከራ (የብልሃትና የብልሃት አልባ) ቡድን ተማሪዎችን ድህረትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት በተለመደው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩት የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ውጤትጋር ተቀራራቢ መሆኑን አሳይቷል። ይህም ውጤት Griffiths (2004) እና O'malley & Chamot (1990) ጥናት አእምሯዊ ብልሃቶች የተለያዩ የትምህርት ተግባራትን በራስ ለመስራት ስለሚያስችል በአዳዲስ ፅንሰ ሀሳብ ላይ የተለያዩ ተግባራትን በመፈፀም በትምህርቱ ሂደት መነሳሳት እንዲኖራቸው ያደርጋል የሚለውን ሀሳብ ይቃረናል።

ሶስተኛው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መረጃውም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል። የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም በአዕምሯዊ ብልሐቶች የታገዘ የማንበብ ትምህርት የተማሩት ሁለቱ የሙከራ ቡድኖቹ የብልሃትና የብልሃት አልባ ቡድን ተማሪዎችን ድህረትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናና ድኅረትምህርት የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት ተቀራራቢ መሆኑን አሳይቷል። ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አእምሯዊ ብልሃቶችን በይዘትነት በመማር መተግበርና በይዘትነት ሳይማሩ መተግበር በአንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ጉልህ ልዩነት የሌለው መሆኑን ነው። የKhezrlou (2012) ጥናት በሁለቱም የሙከራ ቡድኖች መካከል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት ሲኖር በዚህኛው ጥናት በሁለቱም የሙከራ ቡድኖች መካከል ልዩነት እንደሌለ ያሳያል። በመሆኑም ከKhezrlou (2012) ጥናት ከተገኘው ውጤት ጋር ይቃረናል።

በአጠቃላይ አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች የአማርኛ ኢአፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያላቸው በመሆኑ በማንበብ ትምህርት ሂደት ትኩረት ተሰጥቶት በአግባቡ ቢተገበር የተሻለ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል ከተገኘው የመረጃዎቹ የትንተና ውጤት ለመገንዘብ ተችሏል። ሌላው አዕምሯዊ ብልሃቶችን በይዘትነት ከመማር ይልቅ በትግበራ መማር የተሻለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህ አዕምሯዊ ብልሃቶችን በተለያዩ መልመጃች ትኩረት ሰጥቶ መተግበር ያስፈልጋል ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል።

## 6. ማጠቃለያና አስተያየት

የጥናቱ ዋና አላማ አዕምሯዊ ብልሃቶች የአማርኛ ኢአፍፈት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት የማሳደግ ሚና መመርመር` ነበር: ዋና አላማውን መሰረት በማድረግ ሶስት ጥያቄዎችን በማንሳት በብልሃት፣ በብልሃት አልባና በተለመደው የማንበብ ትምህርት አቀራረቦች በሚማሩ 118 ተማሪዎች በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት የፅሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው

ተተንትነዋል። የመጀመሪያውና ሁለተኛው በባለሁለት ተላውጦ ትንተና ልይይት፣ ሶስተኛው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተዋል። ከተገኘው ውጤትና ማብራሪያ በመነሳትም ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል።

1. አዕምሯዊ ብልሃቶችን በተመለከተ ለቋንቋው መምህራንም ሆነ ተማሪዎች ስልጠና መስጠትና የማንበብ ተግባራትንም ብልሃቶችን ለመጠቀም በሚያመች መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በማንበብ ክሂል የማስተማር ዘዴዎቻቸው ውስጥ አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶችን በመጠቀም ቢያስተምሩ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና እራሳቸውን ችለው ራስ መር ሆነው እንዲሰሩ የሚያስችላቸው በመሆኑ በመተግበር እንዲማሩ ማድረግ ያስፈልጋል።
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህር ለመሆን ለሚሰለጥኑ አዲስ ሰልጣኞች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚሰጧቸው ስልጠናዎች ስለአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ጭምር ማስተማርና ማሰልጠን ይጠበቅባቸዋል። በተለይም ሰልጣኞቹ ራሳቸው ብልሃቶቹን የመተግበር ብቃት እንዲኖራቸው ተገቢ ትምህርት በመስጠት ብሎም በክሂሎች የማስተማር ስነዘዴዎች ውስጥ የብልሃቶችን አተገባበር ጭምር በማካተት በእውቀትና በክህሎት የተሻሉ እንዲሆኑ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።
4. የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት ባለሙያዎችና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ለማንበብ ክሂል መማሪያ ምንባቦችን ሲመርጡና የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ሲያዘጋጁ አዕምሯዊ ብልሃቶችን በግልጽ ማቅረብን እንደአንድ የማንበብ ተግባራት ማቅረቢያ መንገድ ቢጠቀሙበት የተሻለ ይሆናል።

## ዋቢዎች


መጋቢው ኃይለማርያም። (2009 ዓ.ም) ። በ*2004* ዓ.ም በተዘጋጀው የ*11*ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች ተነባቢነት ደረጃ (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

ሙሉገበያ ያለው። (2009 ዓ.ም) ። የፅሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳትን ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

በኅሰው የሺዋስ። (2003 ዓ.ም) ። የነባርና የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ንፅፅራዊ ጥናት (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

እንድሪስ አባይ። (2009 ዓ.ም*)* ። በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በአማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅእኖ (ያልታተመ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

ዘውዱ መብሬ። (2008 ዓ.ም)። ሚናለዋጭ ዘዴ የአማርኛ አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትን ችሎታና የማንበብን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋፅኦ (ያልታተመ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት)። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

Anne, R. (2014). Use of Cognitive Reading strategies to Enhance EFL Students Reading comprehension. *International Journal of Education, 2(1), 1-11*

Griffiths, C., & Cansiz, G. (2015). Language Learning Strategies: An Holistic View. *Studies in second language learning and teaching*, *5*(3), 473-493. http//www.doi: 10.14746/ssllt.2015.5.3.7

Chanyalew, E. & Abiy, Y. (2015). Effects of Teacher Scaffading in students' Reading comprehension. *Science, technology and Arts Research Journal, 4(2); 263-271.*

Cohen, A. D. (1999). Language Learning Strategies Instruction and Research. In Cotterall, S. & Crabbe, A. D. (eds). *Learner Autonomy in Language Learning; Definding the field and Effecting change (61-77).* Frankfurt; Peter Lang GmbH.

Cohen, A. D. (1999). Language learning strategies instruction and research. *Learner autonomy in language learning: Defining the field and effecting change*, *8*, 61-68.

Yaman, I. & Cakici, D. (2013). The effect of cognitive and Compensation Strategy Instruction on reading Comprehension skill. Ondokuz Mayis University, Egitim Fakultey; *Jornal of Language and Linguistic Studies; 32(2), 369-384*.

Duke, N. K. & Pearson, (2005). *Effective practices for developing reading comprehension.* In A.E. Farstrup & S.J. Samuels (Eds.), *What research has to say about reading instruction (25-242)*. Newark, DE: *International Reading Association.*

Duke, N. K., & Pearson, P. D. (2009). Effective practices for developing reading comprehension. *Journal of education*, *189*(1-2), 107-122.

Griffiths, C. (2004). *Language-learning strategies: Theory and research* (Vol. 1). AIS St Helens, Centre for Research in International Education.

Harmer, J. (2001). The practice of English language teaching. *London/New York*, 401-405.

Suyitno, I. (2017). Cognitive Strategies Use in Reading Comprehension and Its Contributions to Students' Achievement. *IAFOR Journal of Education*, *5*(3), 107-121.

Khezrlou, S. (2012). Cognitive Strategy Training; Improving Reading comprehension in the Language classroom. Tehran University, Tehran; *The journal of Teaching Language skills; 3(4) 1-22.*

Lau, K. L., & Chan, D. W. (2003). Reading strategy use and motivation among Chinese good and poor readers in Hong Kong. *Journal of Research in Reading*, *26*(2), 177-190.

O'Malley, J. & Chamot, A. (1990). *Learning strategies in second language acquisition*. England, Cambridge University Press.

Oxford, R. (1990). *Language learning strategies*: *What every teacher should know*. Boston, Heinle and Heinle Publishers

Oxford, R. (2003). *Language learning style and strategies*: An overview. Oxford, GALA.

Richards, J. C., & Lockhart, C. (1994). *Reflective teaching in second language classrooms*. Cambridge university press.

Shew, B. (2017). An Assement of factors affecting Student-Teacher Inferenitai understanding in reading comprehension practice; the case of Gilgelbeles College of teachers Education, Benishangul gumuz Region International. *Jorunal of Social Science and Management; 4(2) 148-15*

Teshale, A. and Ymanebirhan, k. (2015). Assessment of The Reading practices of Students; The case of first Year Natural Science Students of bonega College of Teachers Education. *International Jorunal of Educational technology and Research; 6 19-32.*

Ur, p. (1996). *Acourse in Language Teaching Practice and Theory*. 13 printing.

Yussof, Y. M., Jamian, A. R., Roslan, S., Hamzah, Z. A. Z., & Kabilan, M. K. (2012). Enhancing reading comprehension through cognitive and graphic strategies: A constructivism approach. *Procedia-Social and Behavioral Sciences*, *64*, 151-160.